www.abyssinialaw.com

15ኛ ዓመት ቁጥር 1
15th year No. 1

ባህር ዳር ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም
Bahir Dar 13th, Oct.2009

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 13.28 Price Birr	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 70/2002 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ	Regulation No. 70/2009 The Amhara National Regional State Forestry Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation.

ደንብ ቁጥር 70/2002 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደን ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

Regulation No. 70/2009

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FORESTERY ENTERPRISE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com

ክልሉ በደን ልማት ረገድ ያለውን ጂኦ-ኢኮሎጂያዊ አቅም ተጠቅሞ የደኑ ሴክተር ለህዝቡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት መፋጠን የሚፈለግበትን አስተዋጽኦ ማከርከት የሚችልበትን እድል ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

Whereas, it has been necessary that the region, having utilized its geo-ecological potential with regard to forestry development, has to facilitate an opportunity for the forestry sector to enable it to make a contribution, required of it, for the acceleration of the economic and social development of the people therein;

በክልሉ ውስጥ ለሚቀረፁት የደን ልማት ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የደን ሴክተሩ ራሱ በቂ ሃብት የሚያመነጭበትን ተቋም መፍጠር በማስፈለጉ፤

Whereas, it has become necessary to create an institution whereby the forestry sector itself generate adequate resource for the execution of forestry development programs to be formulated in the Region;

በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ለምተው የሚገኙትን የመንግስት ደኖች ለአካባቢው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

Whereas, it has become necessary to properly put to use those public forests which are developed and found at various place in the Region so that they shall make a contribution to the locality with respect to the latter's social and economic development thereof;

በክልሉም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በእንጨትና በእንጨት ውጤቶች አቅርቦትና ፍላጎት መካከል እያደገ የመጣውን ክፍተት ለመሙላት ጠንካራ የደን ልማት ተቋም መፍጠር በማስፈለጉ፤

Whereas, with a view to filling the ever increasing gap between supply and demand in wood and wood products at the regional and national levels, it is necessary to create a strong forestry development institution thereof;

በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እየተበራከተ የመጣውን ሥራ አጥነት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር የሚያስችል ልማት ማካሄድ በማስፈለጉ፤

Whereas, it has become necessary to carry out development efforts that would enable to create a multitude of job opportunities with the view to reducing the ever growing unemployment in all areas of the Region;

በክልሉ ውስጥ ከፉኛ ተራቁቶ የሚታየውን የመሬት ክፍል በደን በመሸፈን የአካባቢ ተሃድሶን ማምጣትና መሬቱን ለተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲውል ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it has been appropriate to bring about an environmental revival and cause the land to be used for better economic benefits by covering that part of the land which is adversely destitute in the region with the afforestation thereof;

www.abyssinialaw.com

በሥራ ላይ ያለው ኋላቀር የደን ልማትና አጠቃቀም ሥርዓት ሳይንሳዊና ቀልጣፋ በሆነ አስተዳደር የሚደግፍ ሞዴል በመፍጠር አሠራሩን ማሻሻልና ዘመናዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክልሉም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ የግሉ ዘርፍ በደን ልማትና ኢንቨስትመንት በኩል የሚያሳየው ተሣትፎ አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የመንግስትን ቀጥተኛ ተሣትፎ የሚጠይቅ ስለሆነ ራሱን የቻለና ንብረትነቱ የክልሉ መንግስት የሆነ የደን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋምና በተወዳዳሪነት እንዲሠራ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ (7) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

Whereas, it has been necessary to revise and modernize the working system by creating a model which may support the existing backward forestry development system in a scientific and efficient administration;

Whereas, due to the fact that the private sector participation in the forestry development and investment is insignificant, when evaluated at the regional and national levels, and it thus requests direct participation of the government, it has been necessary to establish forestry enterprise which is autonomous and owned by the Regional State;

Now, therefore, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provision of art.58, sub. Art. 7 of the Revised Constitution of the National Regional State, hereby issues this regulation.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

PART ONE
GENERAL

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የደን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 70/2002 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This regulation may be cited as "The Forestry Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation No 70/2009."

2. ትርጓሜ፤

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

www.abyssinialaw.com

1. “ቦርድ” ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቋቋመው የኢንተርፕራይዙ ሥራ አመራር ቦርድ ነው።
2. “ቢሮ” ማለት የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ነው።
3. “ደን” ማለት በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው የለሙ በአብዛኛው የዛፎችና ሌሎች የእንጨትነት ጠባይ ያላቸው ተክሎች የሚገኙበት የእጽዋት ክምችት ነው።
4. “ዛፍ” ማለት በዓይነቱ በዕድሜውና በመጠኑ ሳይለይ የእንጨት ጠባይ ያለው ሲሆን ቀርቀሃ፣ ዘንባባና ኤጀንሰው ዛፍ ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ተክል ሊጨምር ይችላል።
5. “የደን መሬት” ማለት ለደን ልማትና ጥበቃ ተብሎ የተከለለና በደን የተሸፈነ አካባቢ የቁጥቋጦ መሬትንና በከፍተኛ ተዳፋት ላይ የሚገኙና የተራቆቱ መሬቶችን ይጨምራል።
6. “የመንግስት ደን” ማለት በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ሥር የዋለ ማናቸውም ጥብቅ ወይም ምርት ሰጪ ደን ነው።
7. “የደን ውጤት” ማለት ዛፍ ወይም የዛፍ ተፈጥሯዊ አካል የሆነ ወይም እንጨት ያልሆነ ማንኛውም ምርት ወይም በመጀመሪያ ደረጃ በሰው እጅ የተመረተ ወይም በፋብሪካ የተዘጋጀ የደን ምርት ነው።

1. “Board” shall mean the managing board of the enterprise to be established in accordance with art. 8, sub-art.1 of this regulation hereof.
2. “Bureau” shall mean the Regional Bureau of Agriculture and Rural Development.
3. “Forest” shall mean a collection of plants in which the majority of trees and other plants of wooden characteristic are found, having either naturally grown or being planted and developed, as the case may be.
4. “Tree” shall mean any such thing that has a characteristic of wood without categorization as to its type, age and size and may include bamboo, palm tree and any plant that the Agency may designate as such.
5. “Forestland” shall mean an area which is reserved for development and protection of forest and thereby covered therewith and may include shrub lands; those areas situated at highly- sloppy and degraded lands.
6. “Government Forest” shall mean any reserve or productive forest which is under the ownership of the Regional State.
7. “Forest Product” shall mean any product of a tree or natural part thereof or a non-wood one or a forest product manually made on a primarily level or processed by a factory.

www.abyssinialaw.com

ክፍል ሁለት

ስለ ብሔራዊ ክልሉ የደን ኢንተርፕራይዝ መቋቋም፣ ዓላማ፣ ተግባርና ድርጅታዊ አቋም

3. ስለመቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደን ኢንተርፕራይዝ ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዙ" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የክልሉ መንግስት ለሚሰይመው ቦርድ ይሆናል።

4. መነሻ ካፒታል

1. ኢንተርፕራይዙ በክልሉ መንግስት የተመደበለትን ጥሬ ገንዘብ ብር 76,339,163 (ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሠላሳ ዘጠኝ ሽህ አንድ መቶ ስልሳ ሦስት ብር) እና በዓይነት የመንግስት ደኖችን መነሻ መስሪያ ካፒታሉ አድርጎ ተቋቁሟል።

PART TWO

Establishment, Objective, Duties And Organizational Structure Of The National Forestry Enterprise

3. Establishment

1. The Amhara National Regional State Forestry Enterprise, / hereinafter referred to as "The Enterprise"/is hereby established as an autonomous government enterprise having its own personality under this regulation.
2. The Enterprise shall be established for indefinite period of time and be accountable to the board to be designated by the Regional State in accordance with art. 8 sub- Art. 1 of this regulation.

4. Initial Capital

1. The Enterprise is hereby established with its initial working capital being Birr 76,339,163 (seventy six million, three hundred thirty nine thousands and one hundred sixty three Birr) allocated for it by the regional government in cash along with the government forests in kind.

www.abyssinialaw.com

5. ዓላማዎች

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ደንና የደን ውጤቶችን በስፋት በማልማት፣ በማምረትና እሴት በመጨመር የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማፋጠን፣
2. ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ሥራ አጥነትን መቀነስና የክልሉን ህብረተሰብ ዘላቂ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣
3. በክልሉም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በእንጨትና በእንጨት ውጤቶች አቅርቦትና ፍላጐት መካከል እያደገ የመጣውን ክፍተት ማጥበብ፣
4. ደንና የደን ውጤቶችን እሴት ጨምሮ በማምረት ወደ ውጭ በመላክና ከውጭ የሚገባውን በመተካት የውጭ ምንዛሬ አቅምን ማዳበር።

5. Objectives

The Enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following objectives:

1. To accelerate the economic and social development of the region by extensively developing and producing forest and forest products as well as by increasing value to same.
2. To reduce the level of unemployment and thereby ensure sustainable gains of the Regional Community by creating wider job opportunities.
3. To narrow the ever growing gap between supply and demand in wood and wood product at regional as well as national levels;
4. To enhance foreign exchange capacity by producing forest and forest products, with an increasing value, exporting same and substituting the imported ones.

6. የኢንተርፕይራዙ ተግባርና ኃላፊነት

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ አንቀጽ (5) ሥር እንደተደነገገው የተቋቋመባቸውን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይቻለው ዘንድ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ለማገዶ፣ ለኮንስትራክሽንና ለፋብሪካ ፍጆታ በጥሬ ዕቃ ምንጭነት የሚያገለግሉና

6. Duties and Responsibilities of the Enterprise

The Enterprise shall have the following duties and responsibilities with a view to discharging the objectives specified under art.5 of this regulation hereof;

1. Establish and develop planting sites for various tree species and those ones usable

www.abyssinialaw.com

የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች ተከላ ቦታዎችን ያቋቁማል፣ ያለማል፣

2. በክልሉ መንግስት ይዞታ ስር ከሚገኙት ደኖች ውስጥ ለምርት የሚሆኑትን ተረክቦ ተገቢውን የማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

3. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ደኖች ማልማት የሚያስችል የደን መሬቶችን በመለየት የሚመለከተውን አካለ አስፈቅዶ የማልማት ሥራ ያከናውናል፤

4. የዱር ሙጫ፣ እጣን፣ ባዮፌውልና ኢሰንሻል ኦይል በማምረትና በማዘጋጀት ረገድ የንግድ ሥራዎች ያካሂዳል፤

5. እንጨትንና እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ወደ ተለያዩ የምርት ዓይነቶችና ደረጃዎች የሚቀይሩ ፋብሪካዎችንና ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ምርቱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባል፤

6. የዛፍ ዘር፣ የማስጌጫና ሌሎች የዛፍና ቁጥቋጦ ችግኞችን ያለማል፣ በነዚሁም ይነግዳል፤

7. በእጣንና በሙጫ ዛፎች የተሸፈኑ ደኖችንና የደን መሬቶችን ተረክቦ ዘላቂነት ባለው መንገድ ያለማል፣ ያስተዳድራል፤

8. ከፋብሪካዎችና ከኢንዱስትሪዎች ፍላጐት አንፃር የጥሬ ዕቃ ምንጭነትን መሠረት

for firewood, construction and for manufacturing consumption raw material sources;

2. Take charge of those forests capable of being used for production out of the forests under the ownership of the government and cause same to be utilized and exploited by preparing the appropriate management plan thereof;

3. Having identified those forestlands enabling to develop forests and bring about economic benefits and thereby secured permission from the bodies concerned, carry out development activities thereof;

4. Cary out business activities by producing and preparing wild-gum, incense, bio-fuel and essential oil;

5. Supply the product to domestic and foreign markets by having planted factories and industries capable of processing and altering wood and non-wood forestry products into various kinds and categories of products.

6. Develop the tree species and other decorating tree and shrub seedlings and thereby conduct business with them;

7. Take over those forests covered with incense and gum trees and forestlands, develop and manage same in a sustainable manner;

8. Encourage forestry development efforts to be carried out by farmers, institutions and small scale developers with the view to

www.abyssinialaw.com

ለማስፋት የሚያስችልና በአርሶ አደሩ፣ በተቋማትና በአነስተኛ አልሚዎች በኩል የሚካሄድ የደን ልማትን ያበረታታል፤

9. ከደን ልማትና ከእንጨት ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ኬሚካሎችና ማቴሪያሎች ንግድ ነክ ተግባራትን ያከናውናል፤
10. አዋጭነቱን በማረጋገጥ ደንና የዱን እንስሳትን ልማት መሠረት ያደረገ የኢኮቱሪዝም ሥራዎችን ያካሂዳል፤
11. በደንና በደን ውጤቶች ላይ በሚደረግ ምርምርና ጥናት ይሳተፋል፣ ይደግፋል፤
12. በደን ልማት ሥራዎች ላይ ለተሠማሩ ወገኖች የማማከርና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፤
13. ማሽነሪዎችን፣ ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች ንብረቶችን እንደአስፈላጊነቱ ያከራያል፡ይከራያል፤
14. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ብድሮችን በማጥናት ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
15. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል።

enabling to the expansion of raw material source-base from the standpoint of the demands by factories and industries;

9. Undertake business-related activities as regards chemicals and other materials having to do with forestry development and wood works thereof;
10. Carry out eco-tourism activities on the basis of forestry and wild animals development by ascertaining the feasibility of such activities thereof;
11. Participate in and support the study and research activities to be conducted on forestry and forest products;
12. Render advisory and training services to those engaging themselves in forestry development activities;
13. Lease out or obtain by rent machineries, vehicles and other properties, as deemed necessary;
14. Own property, enter into contracts, as well as sue and be sued in its own name, study and submit medium and long term loans to the Regional Government and implement same up on approval.
15. Perform such activities as are necessary for the attainment of its objectives and other related ones thereof.

www.abyssinialaw.com

7. ድርጅታዊ አቋም

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

1. የሥራ አመራር ቦርድ
2. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና
3. ሌሎች የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል።

7. Organizational Structure

The Enterprise shall, pursuant to this regulation , have the following organs:

1. A managing board;
2. A General manager to be appointed by the Head of the Regional Government and,
3. Other subordinate managers and staff necessary for the work.

ክፍል ሦስት

ስለ ቦርዱ አወቃቀር፣ ሥልጣን፣ አሠራርና ስለ ሥራ አስኪያጁ

PART THREE

STRUCTURE, POWERS, WORKING PROCEDURE OF THE BOARD AND THE MANAGER

8. ስለ ቦርዱ አመሰራረትና የአባላት ጥንቅር

1. የኢንተርፕራይዙን ሥራዎች በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር የሥራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።
3. የቦርዱ አባላት በቢሮው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሰየማሉ፣ ቁጥራቸውም ከአምስት (5) ያላነሰና ከሰባት (7) የማይበልጥ ይሆናል።

8. Establishment and Composition of Board's Membership

1. A managing Board /hereinafter referred to as the "Board"/ that supervises over and coordinates activities of the Enterprise is hereby established under this regulation.
2. The accountability of the board shall be to the Head of the Regional Government.
3. Members of the board shall be designated by the Head of the Regional Government upon their presentation by the Bureau; their number may not be less than five (5), but not exceeding

www.abyssinialaw.com

4. ቦርዱ የራሱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል።
5. የቦርዱ የአገልግለት ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።
6. የቦርዱ አባላት አበል በኢንተርፕራይዙ ተጠንቶ በቢሮው የሚወሰን ይሆናል።

9. ስለ ቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኢንተርፕራይዙን ሥራ አስኪያጅ በመምረጥ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅርቦ ያሾማል፣
2. ኢንተርፕራይዙ የሚመራበትን አጠቃላይ ፖሊሲ በቢሮው አማካኝነት ለርዕሰ መስተዳድሩ አቅርቦ ያፀድቃል፣ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፣
3. የኢንተርፕራይዙን ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣
4. ኢንተርፕራይዙ በሰው ኃይል፣ በመሳሪያና በሥራ አመራር የሚጠናከርበትን መንገድ ይቀይሳል፤
5. የኢንተርፕራይዙ ሃብትና ንብረት በአግባቡ መያዙንና መጠበቁን

seven (7).

4. The board shall have its own chair-person and secretary.
5. The term of office of the board shall be five years.
6. The allowance of the board members shall be studied by the Enterprise and determined by the Bureau.

9. Powers and Duties of the Board

The Board shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Nominate manager of the Enterprise and submit him/her to the Head of the Regional Government to be so appointed ;
2. Submit the general policy in which the Enterprise is to be managed to the Head of the Regional Government through the Bureau as well as cause the approval; follow up the implementation of same;
3. Review and approve the plan and budget of the enterprise; monitor its implementation thereof;
4. Devise a way through which the enterprise may be strengthened in terms of human resource, material and management thereof;
5. Follow up that the resource and property of the enterprise is properly handled and protected thereof; ensure that its

www.abyssinialaw.com

ይከታተላል፣ የገንዘብና የሰው ኃይል አጠቃቀሙም በዚህ ደንብ መሠረት ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

6. የራሱ ውስጣዊ የሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ያቀርባል።

10. ስለ ቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነሥርዓት

1. ቦርዱ በ3 ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. ከቦርዱ አባላት ሁለት ሦስተኛው በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፣
3. የቦርዱ ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምፁ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

11. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

1. የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ሥር ለኢንተርፕራይዙ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች የማከናወን ሥልጣን ይኖረዋል።

utilization of finance and human resource is compatible with the objectives for which it was established pursuant to this regulation;

6. Formulate and implement its own guidelines of internal working procedure.
7. Submit periodic activity reports to the head of the Regional Government.

10. Meeting Time and Decision Making Procedure of the Board

1. The Board shall convene regular meeting once in three months; provided that wherever it finds it necessary, it may hold an extraordinary meeting at any time;
2. There shall be a quorum where two-third of the members of the board show up at the meeting;
3. Decisions of the board shall be passed through majority vote; provided, however, that, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

11. Powers and Duties of the Manager

1. The manager of the Enterprise shall have powers to perform duties and responsibilities vested to the enterprise under Art.6 of this regulation hereof.

www.abyssinialaw.com

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ ከዚህ በታች የተመለከቱት ልዩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የኢንተርፕራይዙን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ) የኢንተርፕራይዙን የአጭር የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፣ በጀትና የሥራ ፕሮግራም እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በተግባር ላይ ያውላል፤

ሐ) ተጠሪነታቸው ለሥራ አስኪያጁ የሆኑ የኢንተርፕራይዙን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባና ስንበት በሚመለከት ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል፣

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባለው ሕግና በኢንተርፕራይዙ የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፣

2. Without prejudice to the general provision of sub. Art. 1 of this article hereof, the manager shall have the special powers and duties specified herein below:

A. Direct, administer and supervise over the activities of the enterprise;

B. Prepare the short, medium and long-term plan, budget and program of the Enterprise, submit same to the board and put into effect upon approval;

C. Submit to and have appointed by the board the recruitment, assignment and dismissal of the Enterprise's work heads accountable to him;

D. Without prejudice to the provision of this sub. Art. (C) hereof, recruit, administer, promote and dismiss employees, pursuant to pertinent law and administrative rules of the enterprise;

www.abyssinialaw.com

ሠ) የኢንተርፕራይዙን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ የሥራ መዋቅር፣ የሠራተኞችን ደመወዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ረ) የኢንተርፕራይዙን የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ሰ) ኢንተርፕራይዙ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፤

ሸ) የቦርዱን መመሪያዎችና ውሣኔዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤

ቀ) ኢንተርፕራይዙ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚገኘው ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፤

በ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉት ግንኙነቶች ሁሉ ኢንተርፕራይዙን ይወክላል፤

ተ) የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ አጠቃቀም ዘገባዎችን እያዘጋጀ በየሩብ ዓመቱ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቸ) የቦርዱ ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል

ነ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌች ተግባራት ያከናውናል።

E. Organize the office of the enterprise, prepare its working structure, salary and allowance of employees, submit same to the board and follow up its implementation up on approval;

F. Open and operate the bank account of the enterprise;

G. Cause the withdrawal of money in accordance with budget appropriated to the Enterprise and working program and thereby supervise over its implementation thereof;

H. Implement and cause the implementation of the directives and decisions of the board.

I. Supervise that the income to be obtained from the services provided by the enterprise is properly collected thereof;

J. Represent the Enterprise in all relations with the third parties;

K. Prepare and submit to the board quarterly performance and financial reports on quarterly base;

L. Act as a secretary of the board;

M. Perform such other duties as may be assigned to him.

www.abyssinialaw.com

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የኢንተርፕራይዙ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር

1. የኢንተርፕራይዙ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በሃገሪቱ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ መሠረት የሚገዛ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንተርፕራይዙ እንደአስፈላጊነቱ የራሱን የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

13. ስለኢንተርፕራይዙ የበጀት ምንጮች እና የበጀት ዓመት

1. የኢንተርፕራይዙ በጀት የሚገኘው ከሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች ይሆናል።

ሀ) ከክልሉ መንግስት የሚገኝ የመቋቋሚያ ካፒታልና ብድር ፈንድ፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ የሚሰበስባው የአገልግሎትና ሽያጭ ክፍያዎች፣

ሐ) ከፋይናንስ ተቋማት ወይም ከሌሎች ድርጅቶች የሚገኝ የዓይነትም ሆነ የጥሬ ገንዘብ ስጦታ ወይም ድጋፍና

መ) ከሌሎች ምንጮች

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

12. Recruitment and Administration of the Enterprise's Employees

1. The recruitment and administration of employees of the Enterprise shall be governed by the country's labor laws.
2. Without prejudice to the provision stipulated under sub.art.1 of this article hereof, the Enterprise shall prepare and put into effect administrative regulation of its own, as deemed necessary.

13. Budgetary Sources and Fiscal Year of the Enterprise

1. The budget of the Enterprise shall be obtained from the following financial sources:

A. Initial capital and loan fund to be generated from the Regional Government;

B. Service and sales charges to be collected by the Enterprise;

C. Donations in kind or cash or support which the Enterprise may obtain from financial institutions or other organizations and;

D. Other sources.

www.abyssinialaw.com

2. የኢንተርፕራይዙ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል።

14. ስለ የሂሣብ መዛግብት

1. ኢንተርፕራይዙ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ቦርዱ የኢንተርፕራይዙን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝ በተመለከተ ተቀባይነት ያላቸው የሂሣብ አሠራሮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል።

15. ስለ ሂሣብ ምርመራ

ኢንተርፕራይዙ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋናው ኦዲተር ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

16. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

የመንግስት ደኖችንና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በክልሉ መንግስት አማካኝነት ለቢሮውም ሆነ ለሌሎች አካላት ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች የተቆጣጣሪነት ጠባይ ያላቸው ካልሆኑ በስተቀር በዚህ ደንብ አማካኝነት ወደ ኢንተርፕራይዙ ተላልፈዋል።

2. The fiscal year of the Enterprise shall be that of the Regional State.

14. Books of Account

1. The Enterprise shall keep complete and accurate books of account.
2. Wherever it finds it necessary, the board may cause the operation of an acceptable accounting system as of regards the maintenance of books of account and finance related documents of the Enterprise.

15. Auditing

The Books of account and financial as well as property related documents of the Enterprise shall be audited yearly by the office of the Auditor General of the Regional State or by External Auditors to be assigned by the board.

16. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations vested in the Bureau and other organs by the Regional State with regard to the government forests and projects are, with the exception of those having regulatory characters, hereby transferred to the enterprise as per this regulation hereof.

www.abyssinialaw.com

17. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም የክልሉ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖርውም።

18. **መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቦርዱ ያወጣል።

19. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም
አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

17. **Inapplicable Laws**

Any Regional regulation, directive or customary practice, inconsistent with this regulation, may not apply to matters not included in this regulation therein.

18. **Power to Issue Directives**

The board may issue directives necessary for the full implementation of this regulation.

19. **Effective Date**

This regulation shall come into force as of the date of its publication on the Zidre-Hig Gazett of the Regional State.

Done at BahirDar
This 13th day of Oct, 2009
Ayalew Gobezie
Head of Government of the Amhara
National Regional State